| | | |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፫ | በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የወጣ | ADDIS ABABA October 27th, 2020 |

| ማውጫ | Content |
|---|---|
| መመሪያ ቁጥር ፴፬/፪ሺ፲፫ ዓ.ም | Directive No. 34/2013 |
| የኮንስትራክሽን ኦዲት መመሪያ..............ገጽ | Construction Audit Directive |
| | Page............ |

## መመሪያ ቁጥር ፴፬/፪ሺ፲፫ ዓ.ም

## የኮንስትራክሽን ኦዲት መመሪያ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተጣጥመው እንዲቀረጹ፣ ለታለመው ግብ በታቀዱትና በህጉ መሰረት እንዲገነቡ እና በዲዛይኑ መሰረት ለተተለመው የመሰረተ ልማቱ እድሜ እንዲያገለግሉ በተጨማሪም ለኢንዱስትሪው ልማት ምርታማነትና ሁለንተናዊ ትራንስፎርሜሽን በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርጥ ተሞክሮዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በመለየት ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲመጣ እና በስራ ወሰናቸው፣ በጥራት ደረጃቸው፣ በመጠናቀቂያ ጊዜያቸውና በተመደበላቸው በጀት እንዲከናወኑ ለማስቻል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ ዓ.ም አንቀጽ ፲ (፩(ሐ)) እና ፳፪/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲/፪ሺ፲፪ ዓ.ም. አንቀጽ ፳(፫) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ፤

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የኮንስትራክሽን ኦዲት መመሪያ ፴፬/፪ሺ፲፫ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

፩) "ኮንስትራክሽን" ማለት ከመሬት በታችና በላይ የሚከናወኑ የመሠረተ ልማቶችን በዕቃዎች በአገልግሎቶች እና በግንባታ ስራዎች ጥምርታ ህንጻዎች መንገዶች

## Directive No. 34/2013

## Construction Audit Directive

Ministry of urban development and construction hereby issued this directive as per the power vested to it under the proclamation Number 1097/2018 article 22/A and proclamation Number 1210/2020 article 20(3) to ensure that construction projects adapt to the construction industry policies and strategies, Infrastructures are designed to achieve the intended goals and laws in accordance with the design, as well as to ensure the productivity and transformation of industrial and technological development in our country and internationally identifying the best experiences and technologies in order to insure Continous growth, to enable them being carried out according to their project scope, quality standard, completion time and the budget allocation.

### Part One:

### General conditions

**1. Short title**

This directive might be cited as the **Construction Audit Directive No. 34/2020.**

**2. Definition**

Unless otherwise indicated in this term:

1) "**Construction**" means an act includes the creation, expansion, assembly, repair, renovation, upgrading, excavation, demolition

ጥናት የሚያደርግ፣ ሃገራዊ ፋይዳ ባላቸው፣ በሕብረተሰብ ጥያቄ እና ቅሬታ የሚነሳባቸውን የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እና ኦዲት ውጤቶች ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር ማለት ነው።

፰) **"የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት"** ማለት በመንግስት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በጀት መድቦ በባለቤትነት የሚያስገነባቸው ወይም በህዝብና በመንግስት የጋራ ተሳትፎ የሚካሄዱ የግንባታ ፕሮጀክቶች ናቸው።

፱) **"ብክነት"** ማለት በጥራት በተቀባይነትና በምርታማነት ረገድ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውና ፕሮጀክቶች ላይ ከሚጠበቅባቸው መመዘኛዎች በታች የሚያጋጥም አናሳ ውጤታማነት ማለት ነው።

፲) **"የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኦዲተር ወይም ፕሮጀክት ኦዲተር"** ማለት እንደአግባቡ የውስጥ፣ የውጭና የኢንዱስትሪው የሚል ቅጥያ የሚኖረው ሲሆን የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ ሂደታቸው ጀምሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ስር የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን አካል ነው።

፲፩) **"የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት"** ማለት አንድን ውጤት ወይም አገልግሎት ለማግኘት እውቀት፣ ሙያ፣ መሳርያዎችና ቴክኒኮች እንደ ግብአት በመጠቀም ለተወሰነ ጊዜ የሚፈፀም ማንኛውም የኮንስትራክሽን ስራ ነው፣

፲፪) **መምረጥ** ማለት አንድን የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚደረግን ፕሮጀክት ለኦዲት ስራ በናሙና በጥቆማና በጥያቄ መሰረት መለየትና መምረጥ ነው።

፲፫) **ማቀድ** ማለት አንድን ፕሮጀክት የኮንስትራክሽን ኦዲት ለማድረግ ለኦዲት ስራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ እና የቁሳቁስ ግብዓቶችን በመጠቀም ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ያለውን የኦዲቱን ሂደት የሚመራበት የሥራ መርሃግብር ነው።

፲፬) **"ሚኒስቴር"** ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነው፣

፲፭) **"የሚኒስትር መስርያ ቤቱ የኮንስትራክሽን ኦዲት የሥራ ክፍል"** ማለት በኮንስትራክሽን ኢንደስትሪው

implementation of the construction laws, Studies scientifically the inputs and outputs of the before and after construction, audits construction projects that are of National interest, identified by the Ministry, interest of the Public and construction projects and audit results with complaints.

8) **"Government Construction Project"** means construction projects that are fully or partially funded by the government or owned by the public and the government.

9) **"Waste"** means low efficiency in terms of quality, acceptability and productivity in the construction industry and projects.

10) **"Construction Industry/Project Auditor"** has the suffix internal, external and industrial according to its context and from the pre-construction process of construction projects it conducts each activity by this Article sub Article 4.

11) **"Construction project"** means any construction work that is carried out for a certain period of time, using knowledge, skills, tools and techniques as an input to obtain a product or service.

12) **"Selecting"** means identifying and choosing construction projects for construction audit by request, suggestion and sampling.

13) **"Planning"** is the process of conducting the audit process from start to finish using the manpower, financial and material resources required for the audit of a project.

14) **"Ministry"** means the Ministry of Urban Development and Construction;

15) **"Ministry's Construction Audit Department"** means the construction audit department under the Ministry conducts scientific studies implementation of the construction industry policy, implementation

ያለውን የፖሊሲ አፈጻጸም፣የግንባታ ህጎጋት አፈጻጸምን በመፈተሽ እና የግንባታ የፊትዮሽና ኂልዮሽ ግብዓትና ውጤት ሳይንሳዊ ጥናት የሚያደርግ፣ ሃገራዊ ፋይዳ ባላቸው፣ በሕብረተሰብ ጥያቄ እና ቅሬታ የሚነሳባቸውን የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እና ኦዲት ውጤቶች ኦዲት የሚያደርግ የተደራጀ የሥራ ክፍል ነው፡፡

፲፮) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው፡፡

፲፯)በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፲፰) በነጠላ ወይም በብዙ የተገለፀው እንደየአግባቡ ይተረጎማል፡፡

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ፡-

፩) በፌዴራል መንግስት ወይም በፌዴራልና በክልል መንግስታት በጋራ በጀት በሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፤

፪) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የፌዴራል መንግስት ድጋፍ ያላቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፤

፫) ከመንግስት የንግድና የልማት ባንኮች በሚገኙ ብድሮች በሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፤ እና

፬) በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትና እድገት ላይ ተጽእኖ በሚፈጥሩ የአሰራር ስርዓቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፬. <u>የመመሪያው ዓላማዎች</u>**

**፩) <u>ጥቅል ዓላማ</u>**

ሀ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰጡትን ተልዕኮዎች ለመፈጸም የተቀረጹ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የታለሙ ግቦች ለማሳካት የተዘጋጁ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፤ የሬጉላቶሪ ተግባራት፣በመንግስት

of the construction laws, Studies scientifically the inputs and outputs of the before and after construction, audits construction projects that are of National interest, identified by the Ministry, interest of the Public and construction projects and audit results with complaints..

16) **"Person"** means any person who has been granted a natural or juridical right.

17) Any expression in the masculine gender includes the feminine.

18) What is expressed in singular or plural is interpreted accordingly.

**3. <u>Scope of Application</u>**

**This directive applies to the following:**

1. Construction projects to be jointly funded by the Federal Government or the Federal and State Governments, or
2. Construction projects directly or indirectly supported by the Federal Government, or
3. Construction projects to be built with loans from the Government Commercial and Development Banks, or
4. Systems that affect the competitiveness and growth of the construction industry.

**4. <u>Construction Audit Objectives</u>**

1) **<u>General Objectives</u>**

a) Recommend to the Ministry auditing whether the capacity building programs and projects designed to achieve the missions of the construction industry, policies, strategies and targets, the regulatory works and related projects built by the government ownership and related research, development, procurement and

ባለቤትነት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች እና ተያያዥነት ያላቸው የጥናት፣ የምርምር፣ የማዥና የስልጠና አገልግሎቶች በትክክል መተግበራቸውን ኦዲት በማድረግ በአብዛኛው ብክነትን የመከላከልና አሉታዊ ክስተቶች እንዲቀንሱ፣ ምርጥ የአሰራር ስርዓቶችን እንዲስፋፉ መጠቆምና አፈጻጸሙንም መከታተል እንዲሁም በልዩ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምክር ለመስጠት ማስቻል፣

ለ) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በአግባቡ እንዲቀረጹ ለተፈለገው ወይም ለታለመው አላማ እንዲገነቡ እና በዲዛይኑ ለሚገመተው የመሰረተ ልማት ዕድሜ እንዲያገለግሉ ለማስቻል፣ እና

ሐ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ምርታማነት፣ ተወዳዳሪነት፣ ስነ ምግባር፣ በቅንጅት መመራትና የኢንዱስትሪው ዘመናዊነት በቀጣይነት እየተሻሻለና እያደገ መሆኑን በውስጥ ሂደት ትግበራና በኦዲት ማሻሻያ ግብዓት አፈጻጸም ፍተሻ ማረጋገጥ ማስቻል ናቸው።

፪) **ዝርዝር ዓላማዎች**

ሀ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ህጎች፣ የፕሮጀክት አቅርቦት ዘዴዎች ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ፣ የኮንስትራክሽን ቦታ ደህንነትና ጤንነት ሬጉላቶሪ ፍላጎቶችን መሟላታቸውን ለማረጋገጥ፣

ለ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ምርታማ፣ ተወዳዳሪና ዘመናዊ እንዲሆን የተቀረጹ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በአግባቡ መተግበራቸውንና የሚፈልጉትን ውጤቶች ለማምጣቱን ለማረጋገጥ፣

ሐ) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የሀገራችንን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የታለሙ ግቦች

training services are properly implemented and indicating that the best practices be put in place to prevent and reduce the incidence of adverse events and to monitor the implementation and enable take appropriate remedial action.

b) To enable construction projects to be designed for the intended purpose and to be used for the estimated infrastructure age;

c) Ensure that the construction industry's productivity, competitiveness, ethics, coordination and modernization of information management and communication are constantly evolving and enhancing through internal process implementation and audit improvement input performance.

2) **Specific objectives**

a) To insure whether the construction industry rules, project delivery methods, environmental impact, construction site safety and health regulatory requirements are met;

b) To ensure that the construction industry is capable of implementing capacity building programs and projects designed to be productive, competitive and modern.

c) Ensure that construction projects are designed to achieve our country's policies, strategies and goals and are identified in a way that includes stakeholders, women,

ለማሳካት የተዘጋጁና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የተለዩ ለመሆናቸው ማረጋገጥ፣

መ) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቀረጻና በጀት አተካከል ህጎችን አዋጭነትንና የአሰራር ስርዓቶችን አፈጻጸም ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ፣

ሠ) የጨረታ ህጎች፣ አይነቶች ወይም ዘዴዎች ፣ የጨረታ ሰነዶች ይዘትና ፍላጎቶች፣ አስተዳደር ስርዓቶች፣ ሂደቶች፣ ውሳኔዎች አፈጻጸም ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ፣

ረ) የኮንትራክት ህጎች፣ አይነቶች፣ አስተዳደር ስርዓቶች፣ ሁኔታዎች አፈጻጸም ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ፣፣ ሂደቶች፣ የይገባኛል ጥያቄዎች አስተዳደር፣ የጥራት፣ የመጠን፣ የጊዜ፣ የክፍያ፣ የዋጋ፣ የብክነት ደረጃ አፈጻጸም ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ፣

ሰ) በጊዜያዊና በመጨረሻ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ርክክብ ወቅት ለተፈለጉት አላማዎች መጠናቀቃቸውን፣ የዋስትና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በሚሰጥበት ጊዜ ትክክለኛነቱንና ለዲዛይን ዕድሜው ማገልገሉን ማረጋገጥ ናቸው።

**፭. <u>የኮንስትራክሽን ኦዲተር ስነ-ምግባር መርሆዎች</u>**

**የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚያከናውን ኦዲተር የሚከተሉትን የስነ-ምግባር መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ ይገባዋል፡**

፩) በሁሉም የሙያና ስራ ግንኙነቶቹ ለሙያውና ለህዝብ ጥቅም ታማኝ ሆኖ መገኘት፤

፪) በሀላፊነት ስሜትና በትጋት እንዲሁም ቴክኒካዊና ሙያዊ ስታንዳርዶችን በመከተል ሥራውን ማከናወን፤

፫) ሙያዊ አገልግሎቱን ሲሰጥ ከአድልዎ፣ ከጥቅም

youth, children, people with disabilities and the elderly.

d) Ensure the validity of the implementation of the rules and procedures of the construction and budgeting of construction projects.

e) Ensure the validity of bidding rules, types or methods, content and needs of bid documents, management systems, processes, decisions

f) To verify the accuracy of contract laws, types, management systems, conditions, procedures, claims management, quality, quantity, time, payment, price, waste level performance;

g) To ensure that the completed and final construction projects are completed for the intended purpose that they are valid when issuing a warranty certificate and that they have been used for the design age.

**5. <u>Principles of Construction Auditor Ethics</u>**

**The auditor who conducts a construction audit should apply the following ethical principles**

1. Be honest and trustworthy for the public good in all his work and professional relationships;
2. Carry out the work in a responsible and diligent manner and in accordance with technical and professional standards;
3. Free himself from discrimination, conflict of interest and unnecessary influence when

ግጭት እና ከሌሎች ወገኖች አላስፈላጊ ተፅዕኖ ራሱን ነፃ ማድረግ፤

፬) በስራው አጋጣሚ የሚያገኘውን ሚስጥር መጠበቅ፤

፭) ሙያዊ አገልግሎቱን ሲሰጥ በመከላከልና አሉታዊ እንድምታዎችን በመቀነስ፣ ችግሮች ተከስተው ሲገኙ ደግሞ በግልጽና በማያሻማ መንገድ የሚስተካከሉበትን ሀሳብ የመስጠትና ለተግባራዊነቱ ክትትል የማድረግ ፤ እና

፮) በአገር ዓቀፍ ሆነም በዓለም-አቀፍ ደረጃ የተደነገጉ የኦዲተር የሙያዊ ስነምግባሮች ደረጃዎችና መርሆዎችን መተግበር ናቸው::

## ክፍል ሁለት

## የኮንስትራክሽን ኦዲት አፈፃፀም ስልቶች፣ አይነቶችና ደረጃዎች

### ፮. የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚፈፀምባቸው ስልቶች

፩) የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚከተላቸው ቅደም ተከተሎች:-

ሀ/ መምረጥ ፤

ለ/ ማቀድ ፤

ሐ/ በባለቤቱ አግባብ ያለው የስራ ክፍል በሚቀርብ ወይም በሚገኝ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ዶክመንቶች እና / ወይም በምልከታና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በላብራቶሪ ፍተሻ ወይም በልዩ ባለሙያ በኮንስትራክሽን ሳይት የሚከናወን ምርመራ ፤

መ/ የኮንስትራክሽን ኦዲት ዘገባ ስምምነትንና ልዩነትን በግልጽ በማስቀመጥ ማዘጋጀት ፤ እና

ሠ/ ቀጣይነት ያለውና በእቅድ የሚመራ ክትትል ማከናወን ሲሆኑ ቅደም ተከተላቸው መሰረት

providing professional services;

4. Protect the confidentiality of the secret information found during the audit;
5. In the provision of professional services, the main and most important are the prevention and mitigation of negative impacts, and the application of corrective measures and attitudes on special and minor occasions, and
6. Follow National and International auditor professional ethical codes, standards and guidelines.

## Part Two

## Strategies, Types and Standards of Construction Audit Performance

### 6. Strategies for conducting construction audits

1. Construction audit is performed by the following operational audit procedures.

a) To choose
b) Planning
c) Documentation and/or inspection of construction projects provided by the relevant working department or, if necessary, by laboratory inspection or specialist construction site.
d) Prepare construction audit report by clarifying agreements and discrepancies, and
e) Perform continuous and planned follow-up and follow-up investigations;

በማድረግ የሚከናወን ምርመራ፣

፪) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አፋጣኝ ትኩረትና ወሳኝ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው በልዩ ሁኔታ የኮንስትራክሽን ኦዲት ጥያቄ ሲቅርብ ማለትም ከፍተኛ መጓተት፣ ብክነት፣ ያለአግባብ ወጪ መውጣት፣ የጥራት መጓደልና ውጤታማ ያለመሆን ሁኔታዎች ሲከሰቱና የኮንስትራክሽን ኦዲት እንዲደረግ በባለቤቱ ጥያቄ ሲቀርብ በተመረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ሂደቶች ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ምርመራ፣

፫) ብዙሃኑን ተጠቃሚ የሚያደረጉ እና ከፍተኛ በጀት በሚያዝላቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግና በዋና ዋና የፕሮጀክቱ ሂደቶች ላይ በልዩ ሁኔታ በመንግስት ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ምርመራ፣

፬) የኮንስትራክሽን ኦዲት ለማድረግ የሚያስችሉ የክዋኔ ኦዲት እና የኮንስትራክሽን ኦዲት ማንዋሎች ወይም ጋይድላይኖች ቼክ ሊስት በማዘጋጀት፣ በማሳወቅ፣ በማሰልጠን እና እንዲተገበር በማድረግ በእነዚሁ መሰረት የተከናወነን ስራ መነሻ በማድረግ የሚከናወን ምርመራ፣

፭) በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የኮንስትራክሽን ኦዲቱን ውጤታማነት መገምገም ፣

**፯. <u>የኮንስትራክሽን ኦዲት አይነቶችና አፈፃፀም</u>**

፩) የኮንስትራክሽን ኦዲት ከዚህ በመቀጠል ከተዘረዘሩት የኦዲት አይነቶች መካከል እንደአስፈላጊነቱ በመጠቀም ይከናወናል፡፡

ሀ) የውስጥ ኮንስትራክሽን ኦዲተር፣

ለ) የውጭ ኮንስትራክሽን ኦዲተር እና

ሐ) የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኮንስትራክሽን ኦዲተር

2. An audit to be conducted based on selected construction project processes in the event of urgent attention and critical circumstances in the construction projects of special construction audits, such as high delays, wastage, excessive expenditures, poor quality and inefficiency, and upon the request of the owner for a construction audit;
3. An audit that focuses on high-budget construction projects that benefit the masses and is based on the government's request, especially on major project processes;
4. Preparation, notification, training and implementation of manuals or guidelines for operational audit and construction audit checklist based on the work done in this regard;
5. The effectiveness of the construction audit will be evaluated at the end of the fiscal year.

**7. <u>How Construction Audit is conducted</u>**

Construction audit can be carried out in the following types of conduction.

1. Construction Audit uses three types of performance audits as needed. They are:

a) Internal

b) External and

ናቸው።

፪) በብዛትና በቀጣይነት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የሚያስገነቡ ባለቤቶች ወይም በውክልና የሚያስተዳድሩ ተቋማት የውስጥ የኮንስትራክሽን ኦዲተር መኖር ያለበት ሲሆን በተጨማሪም እንደአስፈላጊነቱ የውጭ የኮንስትራክሽን ኦዲተር መጠቀም ይችላሉ።

፫) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በብዛትና በቀጣይነት የማያከናውኑ ባለቤቶች የውጭ የኮንስትራክሽን ኦዲት ለማከናወን ፍቃድ ባለው የውጪ ኦዲትር መጠቀም ይችላሉ።

፬) የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚከናወነው፡-

ሀ/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቀረጻ ሲጠናቀቅ፣

ለ/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ጨረታ ከመውጣቱ በፊት፣

ሐ/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውል ከመፈረሙ በፊት፣

መ/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የጊዜያዊ የመጨረሻና ርክክብ ከመከናወኑ በፊት፣

ሠ/ የዲዛይን ዕድሜውን የሚፈታተን ሁኔታ ሲፈጠር እና

ረ/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በተለያየ ደረጃ ላይ እያሉ እና ከተጠናቀቁ በኋላ እንደአስፈላጊነቱ የኮንስትራክሽን ኦዲት ሊከናወን ይችላል።

፰) **<u>የኮንስትራክሽን ኦዲት ደረጃዎች፣ ማንዋሎች፣ ጋይድላይንና ቼክሊስቶች</u>**

ማንኛውም የኮንስትራክሽን ኦዲት ሥራ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

፩) **<u>የኮንስትራክሽን ኦዲት ደረጃዎች፣</u>**

ሀ/ ለኦዲቱ መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን

c) Ministry's Construction Auditor.

2.Owners or agents who construct large and continuous construction projects are required to have an internal construction auditer and can use an external construction audit as needed.

3.Owners who do not carry out construction projects frequently and continuously may use external construction audits.

4.The construction audit is carried out:

a) Upon completion of production of construction projects;
b) Before the bid floating invitation for the construction projects is undertaken;
c) Before signing construction contracts;
d) Before the provisional and final handover of construction projects and
e) When the design age is challenged.
f) When the construction project at different levels and after finishing of the construction may be audited.

8. **<u>Construction Audit Standards, Manuals, Guidelines and Checks</u>**

Any construction audit work shall have the following;

1. **<u>Steps of Construction Audit</u>**

a) For the preparation of record documents

መመዝገቢያ ሰነዶች የሚዘጋጁበት፣

ለ/ ኦዲተሩ የሚሰየምበት ፣

ሐ/ ኦዲቱ የሚከናወንበት ወይም የሚመረጥበት፣ የሚታቀድበትና በሰነድም ሆነ በመስክ ኦዲቱ የሚደረግበት፣

መ/ ኦዲቱ የሚቀርብበት ወይም የሚዘገብበት እና

ሠ/ የኦዲት ግብዓት አፈጻጸም ክትትል የሚከናወንበትን ደረጃዎች ናቸው።

፪) ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የኮንስትራክሽን ኦዲትን በተመለከተ የሚያወጣቸውን ማናቸውንም የህግ እና የአሰራር ስርዓት ሰነዶች ለኢንዱስትሪው ተዋናዮች፣ ለኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ባለቤቶችና ወኪሎቻቸው፣ ለኮንስትራክሽን ኦዲተሮችና ለሚመለከታቸው ሁሉ አመቺና ተደራሽ በሆነ መንገድ እንዲያውቋቸው ማድረግና አለባቸው።

## ፱. <u>የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚደረግላቸውን ፕሮጀክቶች ስለመምረጥ</u>

የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚደረግላቸውን ፕሮጀክቶች ለመምረጥ:-

፩) ከፍተኛ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፣

፪) ከፍተኛ ስጋት ያለባቸውና የመንግስት ድጋፍ የሚያገኙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች፣

፫) ከ75% በላይ ለሶስት ወር በተከታታይ የተጓተቱና ለመቋረጥ ውለታው የለያቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፣

፬) ከመጠባበቂው (10%) የገንዘብ መጠን በላይ የተጨማሪ ስራ ወይም ክፍያ ጥያቄ በተሰራው ስር መጠን የቀረበባቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፣

for the purpose of the audit;

b) For the designation to the auditor;

c) Where the audit will be conducted or selected, planned and audited by both document and field;

d) where the audit is presented or reported and

e) where the audit input performance is monitored

2.The Ministry shall prepare information to be used as a baseline for the audit inspection and requirements of an audit of each and every construction processes the construction project interest statement of the employer of the projects and the internal auditor, give training and insure their proper usage.

## 9. <u>Selecting projects for construction audit</u>

To select projects for construction audit:

1.Construction projects of great national importance;

2.High-risk and government-funded investment projects;

3.Construction projects that have been delayed and terminated for more than 75% for three consecutive months.

4.Construction projects submitted in excess variation work or works that required additional payments of the reserve amount (10%)

፭) ወደ ሌሎች ፕሮጀክቶች ሊሰፋ የሚችል አወንታዊ ወይም የአፈፃፀም ተሞክሮዎች ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፤

፮) በህዝቡ ወይም በባለድርሻ አካላት ጥያቄ የቀረበባቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች፤

፯) ወቅታዊ የሆኑ አስገዳጅ ሁኔታዎች የተከሰተባቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እና

፰) ከዚህ በፊት በተሰሩ የኦዲት ስራዎች የተሰጡ ግብዓቶችን ማስተናገድ የተሳናቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እና

፱) የኦዲት ሥራዎች በውጭና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ሊመረጡ ይችላሉ።

፲. <u>የኮንስትራክሽን ኦዲት ለሚደረግላቸው ፕሮጀክቶች ዕቅድ ስለማዘጋጀት</u>

የሚዘጋጀው የኮንስትራክሽን ኦዲት ማከናወኛ ዕቅድ

፩) ባለፕሮጀክት ተቋማት

ሀ) የግንባታ ፕሮጀክት ኦዲት ማስደረጊያ ዕቅዳቸውን በየዓመቱ ለሚኒስቴሩ ያሳውቃሉ ወይም በድህረ ገጻቸውም በግልጽ ያሳያሉ፤

ለ) ፕሮጀክቱ ኦዲት የሚደረግበትን ዓይነት ለሚኒስቴሩ ያሳውቃሉ፤

ሐ) በውስጥ ወይንም በውጭ ኮንስትራክሽን ኦዲተሮች የሚያሰሩ ከሆነ የስራ መርሃ ግብራቸውን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይላካል፤

፪) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ

ሀ) በመርሀ-ግብር የተደገፈ የኮንስትራክሽን ኦዲት ማከናወኛ እቅድ ያዘጋጃል፤

ለ) ለስራው አስፈላጊውን ሀብት ይደለድላል፤

ሐ) የኦዲት ማከናወኛ ጊዜውን በግልጽ ለባለፕሮጀክት ተቋሙ ያሳውቃል፤

5.Positive or effective performance experiences that may be extended to other projects or construction projects that have a negative impact

6.Construction projects requested by stakeholders or the public;

7.Construction projects where current mandatory circumstances occur, and

8.Construction projects that do not meet the feedbacks and requirements of previous audits may be audited

9. The ministry and external auditors may choose audit works

**10. <u>Planning for projects construction audit shall be conducted:</u>**

Construction auditing plans shall be:

1. Owners of projects
   a. shall produce their construction auditing plans project shall annually inform the ministry or show on their websites.
   b. shall inform the ministry the type of the audit which will be conducted and
   c. if the audit will be conducted by internal or external construction auditors shall inform their auditing program the ministry
2. The ministry
   a) Shall produce a construction auditing plan with time table.
   b) Shall allocate resources for auditing.

፫) የኮንስትራክሽን ኦዲት ማከናወኛ ዕቅድ የሚከተሉትን ግቦች ለማሟላት የሚያስችል መሆን አለበት፤

ሀ/ የኮንስትራክሽን ኦዲት አላማዎች፣ ስልቶች፣ አይነቶች፣ ቅደም ተከተሎች፣ መርሀ-ግብርና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየጊዜው ለዚሁ ስራ የሚያገለግሉ ሰነዶች በመጠቀም ግቡን ማሳካት፤

ለ/ የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚደረግባቸውን ፕሮጀክቶች አላማዎች፣ ሂደቶችና መርሀ ግብሮች ማሳካት፤

ሐ/ ተገቢ የሆኑትን የኮንስትራክሽን ኦዲት አይነቶች መጠቀም፤

መ/ በኮንስትራክሽን ኦዲት ክንውን ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን በቅድሚያ ተገንዝቦ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ናቸው።

## ፲፩. የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚከናወንባቸው የስራ ዘርፎች

**የኮንስትራክሽን ኦዲት የሚፈፀምባቸው የስራ ዘርፎች ከዚህ በታች የተመለከቱት ይሆናሉ።**

፩) ፕሮጀክቶች ፖሊሲን፣ ስትራቴጂን፣ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ፣ አዋጭነትንና የበጀት ተክላ ስርዓትን በጠበቀ አገባብ መቀረጻቸውን የሚያረጋግጥ ኦዲት፤

፪) ፕሮጀክቶች የጨረታ ሕግን፣ የባለቤትና የተጠቃሚዎችን የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋዊያን ፍላጎት በጠበቀ አገባብ የጨረታ ዶክመንታቸውን ማዘጋጀታቸውን የሚያረጋግጥ የአፈፃፀም ኦዲት፤

፫) ፕሮጀክቶች የጨረታና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎችን መሰረት በማድረግ በባለቤቱና በአማካሪው ወይም በስራ ተቋራጩ መካከል ውለታ

c) Shall transparently inform the owner of the project when the project will be audited.

3. Construction auditing plan should be planned to include the following goals

a. To achieve goals by using construction audit objectives, method, types, steps, programs and other supporting documents the ministry produces

b. To achieve the objectives, processes and scedules of the projects to be audited.

c. Use the appropriate type of the construction audit.

d. To understand, assess and take the appropriate preparation the traits that occur during the construction audit

## 11. Work sectors Construction audit shall be conducted on

The Work sectors where the construction audits are conducted are as follows.

1. Audit to ensure that projects are formulated in a manner that ensures directive, strategy, stakeholder engagement, feasibility and budget implementation
2. Performance audit of projects to ensure that projects are prepared in accordance with the bidding law and the needs of women, youth, children, people with disabilities and the elderly;
3. Performance audit confirming the performance of the contract between the

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Construction

መፈጸሙን የሚያረጋግጥ የአፈፃፀም ኦዲት፤

፬) ፕሮጀክቶች የኮንትራትና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎችና በባለቤቱና በአማካሪው ወይም በስራ ተቋራጩ በተገባው ውስታ መሰረት እየተከናወነ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ የአፈፃፀም ኦዲት፤

፭) ለፕሮጀክቶች የወጣው ወጪ ወይም ገንዘብ እና የስራው መጠንና ዋጋ ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚደረግ ኦዲት፣

፮) የኮንስትራክሽን ሬጉላቶሪ ሕጎች፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች ወይም ደረጃዎች፤ የአቅም ግንባታ ማዕቀፍ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች፤ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ብስለት ደረጃ አፈጻጸም ለማረጋገጥ የሚደረግ ኦዲት እና፣

፯) በናሙና በተመረጡ ፕሮጀክቶች የሰው ኃብቱ ፣የኮንስትራክሽን ግንባታ ግብዓቶችና የኮንስትራክሽን ማሽነሪ መሳሪያዎች ምርታማነት የሚደረግ ኦዲት ናቸው፡፡

## ፲፪. <u>የኮንስትራክሽን ኦዲት ዘገባ አቀራረብ</u>

የኮንስትራክሽን ኦዲት ዘገባ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያሟላ መሆን ይገባዋል፡፡

፩) የኮንስትራክሽን ኦዲት ዘገባ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ሰነዶችንና እንደየአስፈላጊነቱ የሳይት ጉብኝት እንዲሁም የላብራቶሪ ፍተሻና የኤክስፐርቶች ሙያዊ አስተያየቶችን ተጠቅሞ ኦዲት ከሚደረገው ፕሮጀክት ባለቤት ጋር ከኦዲቱ በተገኙ ግኝቶች ላይ ግልጽ ውይይት በማድረግና በሚደረሰው ስምምነትና ልዩነት መሰረት መዘጋጀት ይገባዋል፤

፪) የኮንስትራክሽን ኦዲት ዘገባ ይዘት አጠቃላይ ኦዲት ስለተደረገው ፕሮጀክት አጠር ያለ

owner and the consultant or the contractor in accordance with the bidding and other relevant laws;

4. Performance Audit to ensure that projects are being carried out in accordance with the contract and other relevant laws and the obligations of the owner and the consultant or the contractor.
5. Audit to ensure that the cost or money spent on projects and the amount and value of the work is commensurate with
6. Construction regulatory rules, codes, levels or standards; Capacity building framework programs and projects; To ensure the maturity level of construction project management and
7. Audit of productivity of human resources, construction inputs and construction machinery in selected projects.

## 12. <u>Construction Audit Report Presentation</u>

The construction audit report must meet the following requirements.

1. Construction Audit Report should be prepared using documentation of construction projects and site visits as needed, as well as laboratory inspections and expert opinions, with the owner of the audited project in an open discussion on the findings of the audit and the agreement reached.
2. The content of the construction audit report should provide a brief description of the

| | |
|---|---|
| መግለጫ፣ የኦዲቱ መነሻ ሃሳብና አላማን እንዲሁም ኦዲቱ የተከናወነባቸውን ዘዴዎችንና መስፈርቶች በማቅረብ ኦዲት ለተደረገባቸው ሂደቶች አዎንታዊና አሉታዊ ግኝቶችን ከነመንስዔዎቻቸውና መፍትሄዎቻቸው ጋር በዝርዝር መዘጋጀት ይገባዋል፤ | audited project, the purpose and purpose of the audit, as well as the methods and requirements of the audit, and the positive and negative findings of the audit process with their causes and solutions; |
| ፫) የኮንስትራክሽን ኦዲት ዘገባ የማሻሻያ ሀሳቦች ከአለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ለሀገራችን በሚስማማ መልኩ መቅረብ ይገባዋል፤ እና | 3. Recommendations for the construction of the audit report should be presented in a manner that suits our country from the best of international experience; And |
| ፬) የኮንስትራክሽን ኦዲት ዘገባ የመከላከል፣ አሉታዊ ተጽዕኖን የመቀነስ፣ እና የማስተካከል መርሆዎችን በቅደም ተከተል አክብሮና ቀጣይነት ያለው የማሻሻል ተልዕኮን የሚያረጋግጥ ሆኖ መዘጋጀት ይገባዋል። | 4. The construction audit report should be prepared in accordance with the principles of prevention, negative impact, and corrective action in order to ensure continuous and continuous improvement. |
| **ክፍል ሶስት** | **Part Three** |
| **ተግባርና ኃላፊነት** | **Duties and Responsibilities of Stakeholders** |
| ፲፫. **የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት** | 13. **Duties and Responsibilities of the Ministry** |
| ፩) የኮንስትራክሽን ኦዲት ስራዎች ተገቢውን መርሆዎች ይዘው እንዲከናወኑ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ | 1.Monitor and support the construction audit works in accordance with the relevant principles; |
| ፪) በበጀት አመቱ በሚኒስትር መስርያ ቤቱ የሚከናወኑ የኮንስትራክሽን ኦዲት እቅዶችን እና ግኝቶችን መርምሮ ያጸድቃል፣ | 2.Review and approve audit plans produced by the ministry and findings for the fiscal year; |
| ፫) በሚኒስትር መስርያ ቤቱ የሚከናወኑ ለኦዲት ስራው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል፣ በጀትና ሌሎች ግብዓቶች ያፈላልጋል ይመድባል፣ | 3.Find and assign the required manpower, budget and other resources for the audits executed by the ministry; |
| ፬) ከፍተኛ የሙያ ልምድና ብቃት በሚጠይቁ ውስብስብ የኦዲት ስራዎች ላይ የውጭ አማካሪ የሚቀጠርበትን ሁኔታ ያመቻቻል እንዳስፈላጊነቱም የውጭ ኦዲተር ይቀጥራል። | 4.Facilitate the recruitment of an external consultant for complex auditing tasks that require a high level of professional experience and competence and hire an |
| ፭) የብቃት ማረጋገጫ እያንዳንዱ ኦዲተር ማሟላቱን | |

| | |
|---|---|
| የሚያረጋግጥበት መስፈርት ያወጣል:: የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶቹ በዋናነት መልካም ስነምግባርን፣ ሙያዊ ችሎታንና ጥንቃቄን እንዲሁም አስፈላጊው ነፃነትና ገለልተኝነት በሚያካትት ደረጃ ያዘጋጃል:: | external auditor as needed. 5.Sets the eligibility certification standard for each auditor to meet. The certification requirements are based on primarily ethics, professionalism and caution, as well as the necessary independence and impartiality. |
| ፮) የኮንስትራክሽን ኦዲት አደራረግ ስልጠና በመስጠትና ብቃታቸውን በመፈተን በመስፈርቱ መሰረት አረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለኮንስትራክሽን ኦዲተሮች የሚያገኙበትን ስርዓት ይዘረጋል ፤ | 6.Establish a system for obtaining certification of construction auditors in accordance with the requirements of careful construction auditing and training. |
| ፯) የኮንስትራክሽን ኦዲት አቀራረብ ዘዴንና የኦዲት ግብዓት አፈጻጸም ክትትል ስርዓት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኦዲቱን የመስክ ሥራ ለማከናወን የሚረዳ ጋይድላይን ወይም መስፈርት ያዘጋጃል፤ | 7.Develop a construction audit approach and an audit input monitoring system and, if necessary, a guide or standard to carry out the audit field work; |
| ፰) የኮንስትራክሽን ኦዲቱ የሚከናወንበት ማለትም ኦዲት የሚደረጉት ፕሮጀክቶች የሚመረጡበት፣ ኦዲት ለማድረግ የሚታቀዱበትና በዶክመንትም ሆነ በመስክ ኦዲቱ የሚደረግበት ማንዋሎች ወይም ጋይድላይን እና ቼክሊስት ያዘጋጃል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ በአግባቡ መጠቀማቸውን ያረጋግጣል:: | 8.Prepares, provides training, and verifies that the construction audit will be carried out, ie, the projects to be audited, the plans to be audited, and the documents to be audited in both the document and the field. |
| ፱) የኮንስትራክሽን ኦዲት ሪፖርቱን የሚያቀርብበት አሠራር፤ ቅርፅና ይዘት ምን መሆን እንዳለበት የሚገልፅ የኦዲት ሪፖርት ደረጃ ያዘጋጃል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ በአግባቡ መጠቀማቸውን ያረጋግጣል:: | 9.Procedure for submitting the construction audit report; Develop standards, provide training, and ensure that they are used properly. |
| ፲) የኮንስትራክሽን ኦዲት ግብዓት አፈጻጸም ክትትል የሚከናወንበት ማንዋሎች ወይም ጋይድላይን እና ቼክሊስት ያዘጋጃል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ በአግባቡ መጠቀማቸውን ያረጋግጣል:: | 10. Prepare construction audit input manuals or guideline and checklists, provide training, and ensure their proper use. |
| ፲፩) የሚ/ር መስርያ ቤቱ የኮንስትራክሽን ኦዲት | 11. The Department of Construction Audit and Program shall |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Construction

ቴዎድሮስ ተገኝ ከሣ
የኮንስ/ኢንዱ/አሠራር
ማሻሻያ ቢሮ ኃላፊ

| | |
|---|---|
| ስራዎችና ፕሮግራም የሚመራ የሥራ ክፍል የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤ | have the following duties and responsibilities: |
| ሀ/ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ሕጎችና የአሰራር ስርዓቶች በአግባቡ እየተተገበሩ ስለመሆናቸው የሚረጋገጥበት የኦዲት አሰራር ስርዓት ያዘጋጃል፣ ያስተዋውቃል፣ ስልጠና ይሰጣል ወይም የሚሰጥበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤ | A. Develop, promote, train or facilitate the auditing system of the construction industry to ensure that the policies, strategies, laws and procedures are being properly implemented. |
| ለ/ የኮንስትራክሽን ኦዲት ስራዎች በውስጥ፣ በውጭና በራስ ኦዲተሮች የሚደረጉትን በመለየት ኦዲቱ እንዲተገበር የውስጥ ኦዲተር የሚጠቀሙትን በመለየትና የውጭ ኦዲተር የአሰያየም ስርዓትን በማውጣት ለሁሉም የኦዲት ስራዎች የአመራር ማናውን ይወጣል፤ | B. Construction audit works by identifying internal, external and internal auditors, identifying those used by the internal auditor to implement the audit, and developing an external audit designation system. |
| ሐ/ የኮንስትራክሽን ኦዲተሮች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጫ ስርዓት ይቀርጻል ፣ አግባብ ላለው ክፍል ይሰጣል አተገባበሩንም ይከታተላል፤ | C. Construct the certification system of construction auditors, assign them to the appropriate department and monitor its implementation; |
| መ/ የኮንስትራክሽን ኦዲተሮች የሚሰጡት ግብዓቶች በሙያዊና ሳይንሳዊ መንገድ የተደገፉ ለመሆናቸው ዋቢ መረጃዎችን በመጥቀስ አስተያየቶቻቸውን እንዲሰጡ ያስደርጋል፡፡ | D. Construction auditors will provide references and comments on the fact that the inputs provided are supported professionally and scientifically. |
| ሠ/ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን የሰው ኃይልና የማሽነሪ ምርታማነትን በተመረጡ ፕሮጀክቶች ኦዲት ያደርጋል ፤ውጤቱንም ለሌሎች ጥናትና ምርምር ግብዓትነት እንዲውሉ ያደርጋል፤ | E. Audit the manpower and machinery productivity of the industry with selected projects and use the results as input for other research; |
| ረ/ የፋይናንስ ፍላጎት፣ፍሰትና አጠቃቀም በውለታው በተገለፀውና ለታለመለት ዓላማ የዋለ ስለመሆኑ የኮንስትራክሽን ኦዲት ያደርጋል፣ በኮንስትራክሽን ኦዲቱ የሚገኙ ግብዓቶችንም እንደአስፈላጊነታቸው ለተለያዩ ፖሊሲ ጥናቶች | F. Conduct the construction audit to ensure that the financial needs, flow and utilization are used for the stated purpose, and organize the necessary information to be used for various policy studies as required by the construction audit. |

እንዲውሉ ተገቢውን መረጃ በማደራጀት ለማብዓትነት እንዲውል ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፣

ሰ/ የኮንስትራክሽን ኦዲት የስራ ክፍል ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ የክፍሉ ኃላፊው ሥራውን ውጤታማና ብቃት ባለው መንገድ መከናወኑን ያረጋግጣል፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል።

**፲፬. <u>የኮንስትራክሽን ኦዲተሮች ተግባርና ሀላፊነት</u>**

**የኮንስትራክሽን ኦዲተር ተግባርና ሀላፊነት የሚከተሉትን ያካተታል፤**

፩) የኦዲት ስራዎች ማከናወኛ መርህ ግብር ያዘጋጃል፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያጸድቃል:

፪) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣቸው የኦዲት አሰራር መርሆዎች፣ ስርዓትና ሰነዶች እንዲሁም በጸደቀው መርሃ ግብር መሰረት ኦዲት ያደርጋል።

፫) በኦዲት ስራ ወቅት የሚገኙ የአሰራር ግድፈቶችንና መልካም አፈጻጸሞችን በባለቤቱ በኩል ለሚ/ር መስርያ ቤቱ ያሳውቃል።

፬) ለፕሮጀክቱ አሰሪ እና ለስራ ክፍሉ የኦዲት ሪፖርት ያቀርባል።

**፲፭. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

፩) በኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ሥራ ላይ ተሳታፊ የሆነ በዋናነት ባለቤት ወይም እንደባለቤት የሚሰራና ኦዲት በሚደረገው ፕሮጀክት ላይ ተሳታፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት እንደአስፈላጊነቱ ኦዲት የመደረግ እና ለሚቀርብለት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ አለበት።

፪) ለኦዲት የሚያስፈልግ በጀት ከፕሮጀክቱ ጋር እንዲካተት ማድረግ ይጠበቅበታል።

G. The construction audit department is accountable to the minister and the head of the department ensures that the work is carried out efficiently and efficiently and submits a performance report.

**14. <u>Duties and responsibilities of the construction audit department</u>**

**The duties and responsibilities of the Construction Auditor include:**

1. Shall prepare and present auditing action plans to be approved by the Ministry
2. Shall conduct audits in accordance with the principles, procedures and documents of the Ministry as well as approved action plan.
3. Through the owner shall inform any irregularities and good performances during the audit to the Ministry.
4. Submit an audit report to the project employer and the department.

**15. <u>Duty to cooperate</u>**

1. Any person or organization involved in the construction project that is primarily the owner or owner of the project and is involved in the audited project shall be required to audit as necessary and respond appropriately to the request.
2. The budget required for the audit should be included in the project.

## ክፍል አራት

## ስለኦዲት ሪፖርት፣ መዝጊያና ክትትል

### ፲፮. በኦዲት ስራ ማጠናቀቂያ ወቅት ስለሚከናወኑ ተግባራት

በኮንስትራክሽን ኦዲት ደረጃዎች፣ ማንዋሎች፣ እና ጋይድላይኖች ላይ የኦዲት ሪፖርት ዝግጅት፣ መዝጊያና ክትትል በተመለከተ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የኦዲት ስራው እንደተጠናቀቀ ኦዲተሩ ከኦዲት ተደራጊው ጋር የመጨረሻ የመዝጊያ ስብሰባ ማድረግ የሚኖርበት ሲሆን የሚከተሉትን ሂደቶችም ግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት:

፩) የኦዲት ምርመራው ውጤት ከኦዲቱ ዓላማ እና መርህ አንጻር መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፤

፪) የኦዲት መዝጊያ ውይይቱን ቃለ-ጉባኤ መያዝ ያለበት ሲሆን፤ በኦዲቱ ግኝት ላይ ወይም ኦዲተሮቹ በተከተሉት ዘዴ ኦዲት የተደረገለት ፕሮጀክት ባለቤት የተስማማባቸውንና ያልተስማማባቸውን ነጥቦች እንዲሁም የሚያነሳቸውን ምክንያቶች በፅሑፍና በድምፅ መያዝ አለበት።

### ፲፯. ስለኦዲት ሪፖርት ይዘትና ቅርፅ

የኦዲት ሪፖርቱ ይዘት የምርመራውን ዓላማ፤ የምርመራውን ሽፋንና ውጤት ግኝቶችን፤ መደምደሚያዎችን፤ አስተያቶችን እና የማሻሻያ ሀሳቦችን መያዙ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት:

ሀ) ኦዲት የተደረገለት ፕሮጀክት ስም፣

ለ) የኦዲት ምርመራ ጽሁፉን ይዘት ወይም አላማ የሚያስረዳ ርዕስ ወይም መግለጫ፣

ሐ) በኦዲቱ የተሸፈነው ጊዜ

## Part Four

## About Audit Report, Closing and Monitoring

### 16. Activities during the completion of the audit

As described above Preparation, closing and monitoring of audit report on construction audit standards, manuals and guidelines the Auditor General shall hold a final closing meeting with the Auditor General as soon as the audit is completed and the following procedures shall be considered.

1. Ensure that the results of the audit are conducted in accordance with the purpose and principles of the audit;
2. The closing of the audit session should include; the findings of the audit or in the manner prescribed by the auditors, the owner of the audited project shall record points of agreement and disagreement and as well as the reasons for the disagreement Reasons in writing and voice record.

### 17. Content and Format of the Audit report

The content of the audit report is the purpose of the investigation; Findings and findings of the investigation; Conclusions: It should include the following information, as well as comments and suggestions for improvement

1. Name of the audited project;
2. Title or description of the content or purpose of the audit document;
3. The time covered by the audit:

መ) የአዘጋጁንና የኦዲተሩን ስም፤ ዝግጅትና ግምገማ ከተደረገባቸው ቀናት ጋር፤

ሠ) የመለያ ሚስጥራዊ ቁጥር'

ረ) ኦዲተሩ በኦዲት ዘገባው የእያንዳንዱ ገፅ ላይ መፈረም አለበት::

፲፰. <u>ስለኮንስትራክሽን ኦዲት ሪፖርት አቀራረብ</u>

በኦዲት ሪፖርቱ አቀራረብ ወቅት ኦዲተሩ ከዚህ ቀጥለው የተመለከቱት ሂደቶች መከተል ይኖርበታል፦

፩) የኦዲት መዝጊያ ስብሰባው እንደተጠናቀቀ ዝርዝር ሁኔታዎችን ያካተተ የተሟላ ሪፖርት በማዘጋጀት ለኮንስትራክሽን ኦዲት የስራ ክፍል ማቅረብ፣ እና

፪) በሚመለከተው አካል የፀደቀውን ሪፖርት ኦዲት ለሚደረግለት ፕሮጀክት ባለቤት መላክ ናቸው::

፲፱. <u>በኦዲት ግኝቱ ሪፖርት መሰረት ስለሚደረግ ክትትል</u>

የኮንስትራክሽን ኦዲት የስራ ክፍሉ በኦዲት ግኝቱ ሪፖርት መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ተገቢውን ማስተካከያና እርምጃ መወሰዱን እንዲሁም የተወሰደው እርምጃ የተፈለገውን ውጤት ማስገኘት መቻሉን ይከታተላል፣ በቀጣይ ኦዲት እንዲታይ ያስደርጋል::

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳. <u>ለኦዲት ስለሚፈፀም ክፍያ</u>

ከኦዲት ስራ ጋር በተያያዘ የሚወጡ ወጭወችን በተመለከተ:-

፩) የውጭ ኦዲተር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኦዲት ከሚደረገው ፕሮጀክት ባለቤት ጋር በሚደረስ ውል ይፈጸማል፤

4. Name of the Editor and Auditor፤ With dates of preparation and review;
5. Account password
6. The auditor must sign each page of the audit report.

**18. <u>Presentation of Construction Audit Report</u>**

During the presentation of the audit report, the auditor must follow the following steps

1. Prepare a complete report to the Construction Audit Unit at the end of the audit closing session;
2. Send the report approved by the relevant body to the owner of the audited project.

**19. <u>Monitoring based on audit findings</u>**

The Construction Audit Unit will monitor the corrective action taken in accordance with the recommendations made in the audit findings and ensure that the action taken achieves the desired results.

## <u>Part Five</u>

## <u>Miscellaneous provisions</u>

**20. Payment for audit**

Regarding audit costs:

1. The external auditor when necessary shall enter into an agreement with the owner of the project to be audited;
2. When there is a fee for laboratory testing, it will be handled in accordance

| | |
|---|---|
| ፪) ለላብራቶሪ ፍተሻ የሚያስፈልግ ክፍያ ሲኖር በፕሮጀክቱ ውስታ መሰረት ይስተናገዳል፤<br>፫) ልዩ ባለሙያ ኦዲቱ ባስፈለገ ጊዜ ኦዲት ከሚደረገው ፕሮጀክት ባለቤት ጋር በሚደረስ ስምምነት ተፈጻሚ ይደረጋል፤<br>፬) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ለሚደረጉ ኦዲቶች በራሳቸው በጀት የሚሸፈን ይሆናል፣<br>፭) በውስጥ ኦዲተሮች ለሚደረጉ ኦዲቶች ኦዲት በሚደረግለት ፕሮጀክት ባለቤት በጀት ይሸፈናል፣ | with the project contract;<br>3. The audit shall be carried out by agreement with the owner of the audited project when necessary.<br>4. The audits conducted by the minister office auditors and the supervising authority shall be covered by their own budget.<br>5. The budget of the project audited by the internal auditors shall be covered by the budget of the owner. |
| **፳፩. ኦዲት የሚደረግለት ፕሮጀክት ባለቤት ግዴታ** | **21. Duty of the owner of the audited project** |
| የኮንስትራክሽን ኦዲተር ቀጥሮ የሚያሠራ ባለቤት፡-<br>፩)ማንኛውም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ባለቤት ከፕሮጀክቱ ጋር በሚመርጠው የኮንስትራክሽን ኦዲት ዓይነት የተመጣጠነ በጀት መያዝ ይኖርበታል፣<br>፪) ለኦዲት ሥራ የተመረጠ በመንግስት ፋይናንስ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚሰራ ማንኛውም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ባለቤት ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ ዶክመንቶች ወይም ሰነዶች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣቸው የኦዲት የአሰራር ስርዓት ማንዋሎች፣ ጋይድላይንና ቼክሊስቶች መሰረት ለኦዲተሮች አዘጋጅቶ የማቅረብ ግዴታ አለበት።<br>፫) የኮንስትራክሽን ኦዲተር ቀጥሮ የሚያሰራ ባለቤት በፕሮጀክቶች ላይ የሚገኙ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ግኝቶችን ለባለቤቱና ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ ኃላፊነት ይኖርበታል፣<br>፬) የቀጠረውን የኮንስትራክሽን ኦዲተር ውል ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመላክ ኃላፊነት ይኖርበታል፣ | Owners who hires a construction auditor<br>1) Every construction project owner should have a budget that is commensurate with the type of construction audit he or she chooses.<br>2) Any construction project owner who is selected for audit work, fully or partially funded by the Government, shall submit the required documents or documents to the auditors in accordance with the audit procedures, guidelines and checklists issued by the Ministry.<br>3) The owner shall be responsible for notifying the owner and the ministry of any positive or negative findings on the projects.<br>4) It shall be the responsibility of the Construction Auditor to send a report to the Ministry on the performance of the contract. |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Construction

፭) የቀጠረውን የኮንስትራክሽን ኦዲተር ኃላፊነቱን በገባው ውል መሰረት ስለመወጣቱ የመልካም ስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመላክ ኃላፊነት ይኖርበታል፣

## ፳፪. ተጠያቂነት

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ኦዲት አድራጊው አካል ከኮንስትራክሽን ኦዲት ጋር በተያያዘ በዚህ መመሪያና በሌሎች ህጎች መሰረት የሚወስዷቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

፩) ማንኛውም ኦዲት ተደራጊ ተቋም፡-

ሀ) ለኦዲት ስራው አስፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶችን ለኦዲት አድራጊው አካል ላለመስጠት በማሰብ ሆን ብሎ የደበቀ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) ትክክለኛ ውጤት እንዳይገኝ ለማድረግ በማሰብ ሆን ብሎ መረጃዎችን የቀየረ፣ የሰረዘ ወይም የደለዘ እንደሆነ አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ መሰርት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪) ማንኛውም ኦዲተር፡-

ሀ) የኦዲት ተደራጊውን ጥፋቶች ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያለፈ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የግል ጥቅሙን ለማስጠበቅ በማሰብ በህዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ እንደሆነ አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፫) ማንኛውም የኮንስትራክሽን ኦዲት ስራዎች ግኝቶች በመንግስት ፀድቀው ግልጽ እስከሚደረጉ ድረስ መረጃዎቹ በሚስጥር መያዝ አለባቸው፡፡

5) The owner shall be responsible for forwarding performance report in accordance with the contract of the hired construction auditor who was

## 22. Accountability

Administrative measures to be taken subject to the provisions of this Directive and other laws by the Ministry of urban development and construction and the auditing body measures taken by shall:

1. Any audit institution

A. Deliberately concealing documents necessary for the audit; Or

B. He will be held liable under applicable criminal law if he deliberately alters, deletes or deletes information in order to prevent an accurate result.

2. Any auditor will be

A. whether the auditor's intentions were intentional or negligent; Or

B. He shall be liable in accordance with applicable criminal law for the purpose of harming the interests of the public and the government for the protection of his personal interests.

C. The details of any construction audit work shall be kept confidential until the findings are approved by the government.

**፳፫. <u>ማንዋሎች፣ ጋይድላይንና ቼክ ሊስት ስለማዘጋጀት</u>**

፩) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መመሪያውን ለማስተግበር የሚረዱ ማንዋሎች፣ ጋይድላይንና ቼክ ሊስቶች ያዘጋጃል፡፡

፪) ክልሎች በዚህ መመሪያ መሰረት ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የተቃኘ የኮንስትራክሽን መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

፫) ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፬. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

ከዚህ ቀደም የነበሩ ልማዳዊ አሰራሮች እና በኮንስትራክሽን ኦዲት የወጡ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

**፳፭.<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሊያሻሽለው ይችላል ፡፡

**፳፮. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከ__________ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ወ/ሮ አይሻ መሀመድ (ኢ/ር)
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን
ሚኒስቴር ሚኒስትር

**23. <u>Preparing Manuals, Guideline and Checklist</u>**

1. The Ministry shall prepare manuals, guidelines and checklists to implement the directive.
2. States may issue construction guidelines based on their own circumstances in accordance with this Directive.
3. Any directive or customary law concerning laws that do not apply shall not apply to matters covered by this Directive.

**24. <u>Transitory provison</u>**

Previous practices and guidelines issued by the construction audit are hereby repealed.

**25. <u>Improving the directive</u>**

The Ministry may amend this directive when it deems it necessary.

**26. <u>Duration of the Directive</u>**

This directive shall enter into force from the date of __________/2020.

Mrs. Aisha Mohammed (Eng.)
Minister of FDRE Minstry of Urban
Development and Construction